# የነፃነት ምልክት የነበሩ ተራሮች በወያኔ ተናዱ፤ ኢትዮጵያውያን ኩራታቸውን መሸጥ፣ በደል መሸከም ለመዱ፡፡

ዘንድሮ አንድ ቢበዛ ከሁለት የማይበልጡ ግለሰቦች ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን ፀንቶ የኖረውን ኢትዮጵያዊ መልክዓ - ምድር ጭምር ጤና እየነሱት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ተራሮች በቅናት መጠበቁ ቀርቶባቸው «እናንተም የእኩልነት፣ የነፃነትና የአይበገርባይነት ዓርማ ሆናችሁ ልትኖሩ አትችሉም» ተብለው እየታወኩ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኩራት ምልክት ሆነው ጠላትን ቁልቁል ይጠብቁ የነበሩ ተራሮች፣ ከራሡ በተወለዱ ልጆች ጠላት ሆነው እየተሸጡ ነው፡፡ የመናዱና የመሸጡ ተግባር መቼ እንደተጀመረ በደል መሸከም ባህሉ ማድረግ የጀመረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተዘነጋው ሰንብቷል፡፡ እዚህ ላይ አንዳንዶቹን ማስታዎሱ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ወያኔ ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ ቁጢጥ ባለ ማግሥት ሳይፈራ ማንንም ለመጠየቅ ሳይጨነቅ የኢትዮጵያን የባሕር በር በሻዕቢያ አሻሻጭነት ለአረብ ሸጧል፡፡

የኦሞን ወንዝ በመዘወር ለመስኖ ተግባር ለማዋል ተጀምሮ የነበረውን እንቅስቃሴ፣ የቱርካናን ሐይቅ ውሃ የጨው መጠን ይጨምራል፤ ለዓሣዎቹና ለሌሎች በሐይቁ ውስጥ ላሉ ነፍሳት ጉዳት ያስከትላል ብላ ኬንያ ስለተቆጣች በልመና በእጅጉ የሚተማመነው የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት የልማቱ ተግባር በአስቸኳይ እንዲቆም አድርጓል፡፡ ከዚያ በፊት ወያኔ ገና ዱር እያለ ከኢጣሊያ መንግሥት በተገኘ ብድር የበለስን ወንዝ ለመስኖና ለኃይል ማመንጫ ሥራ ለማልት ተጀምሮ የነበረውን አበራታች እንቅስቃሴ ከሱዳንና ግብጽ መንግሥታት በተሰጠ ትዕዛዝ ኢጣልያዊ መሐንዲሶችን በማገት ሥራው እንዲቆም አድርጓል፡፡ በዚህም በራስ መተማመንና ሕዝብን ከረሃብና ከልመና ውርደት ለማዳን የነበረውን ዕቅድ ለራሱ የፖለቲካ ዓላማ ሲል እርግፍ አድርጎ ከመተውም ባሻገር አገራችን በወንዞችዋ የመጠቀም መብትዋን ለኬንያ፣ ለሱዳንና ለግብጽ ሸጧል፡፡ ይህ ሁሉ ተዘንግቷል፡፡

ወያኔ ሥልጣን እንደያዘ ሥራውን የጀመረው በብዙ ዓሥርተ-ዓመታት የተገነባውን አገር ጠባቂ ሠራዊት በመበተን ነበር፡፡ ይህ ብተና አንዳንድ ሰዎች እንደሚያስቡት ሠራዊቱን በመፍራት ወይም በመጥላት አልነበረም፡፡ ዓላማው አገርንና ሕዝብን ጠባቂ ለማሳጣት በማቀድ ከወያኔ እኩይ አእምሮ የመነጨ ነው፡፡

የኩራታችን ዓርማ፣ የሕልውናችን መሠረት የሆነውን የኢትዮጵያ ምድር ወያኔ ለሱዳን ከመሸጡ በፊት፣ መሸጥ የጀመረው የአገሪቱን ብሔራዊ ሚሥጥርና ገበና ነበር፡፡ ወያኔ አዲስ አበባ እንደደረሰ የሱዳን ቱባ ሰላዮች በሙሉ ውሎ አዳራቸው ከኮ/ል ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ቢሮ ውስጥ ከአቶ ክንፈና ከአቶ ሐሰን ሽፋ ጋር ነበር፡፡ የወታደራዊ ኢንዱስትሪዎችን ሚሥጥር ለሱዳን ገልቦ ከማሳየት ጀምሮ ለሃምሣ ዓመታት የተገነባውን የአየር ኃይል ተቋም፣ ለሻዕቢያ በስጦታመልክ ሲያስረክብ፣ ለሱዳን ደግሞ ሸጧል፡፡

ቅንጅትና ሌሎችም በሕዝብ ውሳኔ ድል በተቀዳጁበት፣ ወያኔ ርዶ መግቢያ ጠፍቶት በነበረበት ወቅት፣ የኢትዮጵያ ሕልውና የሚያሳብዳቸውን «ድርጅቶች» እየጠራ «ምነው የት ጠፋችሁ? ነፃነት ስትሉ፣ እንገነጠላለን ስትሉ አልነበረምን? ይልቁንስ ከመሄዴ በፊት ያለምንም ቅድመሁኔታ የምትፈልጉትን ላድርግላችሁ» በማለት አገሪቱን ለመሸጥ ጥሪ አቅርቦ እንደነበርና ወያኔ ምን ያህል አደገኛና በአጥፍቶ ጠፊ ግለሰቦች የሚመራ እንደሆነ ዘንግተናል፡፡ በደልን ፈጥኖ የመርሣት አዲስ ባህል!!

ወያኔ የጀመረውን ኢትዮጵያን የማዋረድ፣ ክብርዋን የመግፈፍና መሬቷን የመሸጥ ተግባር ገፍቶበት እነሆ ዛሬ ደግሞ የኩራትና የነፃነት ምልክት የነበሩ ተራሮቿን ከሰሜን እስከ ደቡብ ገምሶ ለሱዳን ሰጥቷል፡፡



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ቴዎድሮስ እያገሣ ያደገበትን፣ አፄ ዮሐንስና ሌሎች የኢትዮጵያ ጀግኖች ደማቸውን፣ ዮሐንስ ያፈሰሰበትን መሬት ታሪክንና ሕዝብን፣ ይህም ቢቀር ደግሞ እግዚአብሄርን ሣይፈራ ወያኔ ከላይ እስከታች ጎምዶ ለሱዳን ሰጥቷል:: ይህንንም ለማረሳሳት እየሞከረ ነው::

ታላቁ የአፍሪካ ጄኔራል ራስ አሉላ አባ ነጋ ሲሞቱ አብሮአቸው የነበረና ምኞታቸውን በቅርብ የሚያውቅ ታማኝ አሽከራቸው ካወረዳቸው ሙሾዎች አንዱን በሐጊ ኤልሪሽ በእንግሊዝኛ ከተጻፈው የራስ አሉላ ታሪክ ከትግርኛው ወደእንግሊዝኛ ከዚያም ከእንግሊዝኛው ወደ አማርኛ የተመለሰው እንዲህ ይነበባል:-

አንተ ነህ ወይ የሞትከው?
ማነው የገደለህ አባ ነጋ?! ድል አብሣሪ፣
እንደ ዘንዶ ተወናጫፊ፣
እንደ በረሀ እባብ ተወርዋሪ፣
እንደ አንበጣ ገደል አፋፍ ሠፋሪ፣
ክንድህ የአንበሣ ወገብ ሠባሪ፣
<u>የከሠላ ባል</u>፣ የባሕር ዘበኛ
<u>ባህር አፍቃሪ</u>::

እንዲህ የተባለላቸው ጀግኖች ልጆች ዛሬ በወያኔ ተወክለው ከሠላና የባሕር በር ሊታያቸው ቀርቶ የኢትዮጵያን ለም መሬትና ማዕድንዋን በመሸጥ አላበቁም:: የክብራችን፣ የነፃነታችንና የባህላችን ዘበኛ ሆነው የኖሩትን ተራሮች እየሸጡ ነው፤ «እበት ትል ይወልዳል!»

ይህን አሳፋሪ ተግባር ከፊላችን ዝም ብሎ የመራብ፣ ዝም ብሎ የመታመም፣ አዲስ በመጣ የተበዳይነት ባህል ተቀፍድደናል ( Victim Culture):: ይህ ሁሉ በደል በአገር ላይ ሲወርድ እያየን ዝም ብለን እየታመምን፣ ዝም ብለን እየሞትን ነው:: ሌሎቻችን ደግሞ ከወያኔ በሚገኝ ፍርፋሪ፣ ጥቅማ ጥቅም ረክተንና የሆነው ይሁን ብለን «በምግብ ለሥራ» ተደልለን ለአገር ሻጩ ወያኔ አድረናል:: በትንሽ ጥቅም የሚደለሉ ዳግሞ ሕፃናት ወይም የሕፃን አእምሮ ያላቸው ናቸው:: ሕፃናት የተሻለ ነገር እንዳለ ስለማያውቁ በትንሽ ነገር ቢደለሉና ቢረኩ አይፈረድባቸውም:: እያወቀ አገርን የሚያህል ከሚሸጥ ነጋዴ ጋር ተባብሮ በሚገኝ ጥቅም የሚደለሉ ግን የሕፃናት ሕፃናት ናቸው:: የሚገርመው ግን እነደዚህ ሆኖ አለሁ እያሉ መኖር መቻሉ ነው:: «ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል» እንደሚባለው::

አገር እየሞተ፣ ትውልድ በዓለም ሕዝብ ፊት ዝቅ ብሎ እየታየና እየተዋረደ፣ ዜጋ ዞሮ መግቢያ አገር እያጣ የሚኖር ኑሮ ግን፣ ባገኙት ረክተው ከሚደሰቱ ሕፃናት፣ በውርደት ሞተው መቃብራቸው ከሚሞቃቸው በታች መሆን ነው:: የነፃነት ምልክት የነበሩ ተራሮች እየተናዱ፣ በደልን ተሸክሞ መኖርን መልመዱ የትውልድ ውርደት ነው::

መቸም ቢሆን ታሪክ የማይረሳው አኩሪ ሥራ በመሥራት ያለፉ ጀግኖቻችንን በየአደባባዩ እያነሳን በእነርሱ ታሪክ መኮፈሱ አንድ ቦታ ላይ ቆም ብሎ፣ የትናንትናው ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስ፣ አሉላ፣ ምኒሊክ፣ አብዲሳና ሌሎችም አርበኞች ከዚህ ትውልድ መካከል መወለድ ይኖርባቸዋል:: በአባቶቻችን ክቡር መስዋዕትነት ዳር ድንበሯ ተከብሮ ለዚህ ትውልድ የተላለፈችልንን ሀገራችን ከተጋረጠባት አደጋ ተከላክሎ የማዳን ግዴታ ለማንም በይደር የሚተላለፍ ሳይሆን የዚህ ትውልድ ግዴታ መሆኑን አውቀን ሀገራችንና ሕዝባችንን ለመታደግ ሁላችንም በያለንበት በቁጭት ልንነሳሳ ይገባል::

**ከኢትዮጵያ የድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በለንደን**
**ጥቅምት 2001 ዓ.ም.**



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com